የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

# ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) የቀረበ የቀጣይ ትግል ጥሪ

## በሕዝብ ሰማዕትነት የተሰበረው የጥፋት አዙሪት መልሶ እንዳይገጥም "ዜጎች ለግንቦት ድሎች" ብለን እንሰባሰብ

የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ አንዴ በገዥዎች የጥቅም ግጭት፥ ሌላ ጊዜ በብሔሮችና በጠቅላላው ሕዝብ የኀልውናና የመብት ተጋድሎ፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ የውጭ ወራሪዎችን ጥቃት ለመቋቋም በተካሄዱት የክብርና የብሔራዊ ነፃነት ትንንቆች የተነሳ ባልተቋረጡ የጦር ግጭቶች ለዘመናት ሲዋከብ የኖረ ኅብረተሰብ ነው:: በዚህ ጊዜና ታሪክ ተጋግዘው በጎዱት ኅብረተሰባችን ውስጥ ኢትዮጵያውያን በሙሉ የሰላም ፋታ፥ የዴሞክራሲና የማኅበራዊ ፍትኅ ፍንጭ ተነፍገው ለዘመናት በመቆየታቸው አገራችን የርሃብ፥ የስደት፥ የኋላ-ቀርነትና የጭቆና ቋት ሆና እንደቀረች ለሁላችንም ግልጽ ነው:: ድህነት፥ የዴሞክራሲ መጥፋት፥ መራቆትና የማኅበራዊ ፍትኅ መጓደል የሚቀሰቅሷቸው ግጭቶች መልሰው ድህነታችንንና ጭቆናን እያባባሱ፥ የማኅበራዊ ፍትኅን ደብዛ እያጠፉ፥ ይኸ ደግሞ በተራው ሁኔታዎችን ለሌሎች ግጭቶችና ጦርነቶች እያመቻቸ ኅብረተሰባችን እንደዚህ አውተብትበው እጅ ከወርች ካሰሩት የጥፋት አዙሪቶች ለመላቀቅ የሚያስፈልገውን ፋታ ሳያገኝ ለዘመናት ቆይቷል::

የእነዚህ የጥፋት አዙሪቶች መከማቸት ጠንቅ የማኅበራዊና የኤኮኖሚ ድቀታችን ብቻ አይደለም:: በፖለቲካው መስክ አመፅን እንደ መደበኛ የመጀመሪያ አማራጭ የልዩነት መፍቻ መሣሪያ አድርጎ የሚያይ አስከፊ ባህል በኅብረተሰባችን ሰርፆ እንዲገባ አድርጓል:: በአገሪቱ ለሚከሰቱ የፖለቲካ ልዩነቶች ሁሉ አማራጭና አስታራቂ መፍትሔ ሳይፈልጉ የመሣሪያ ግጭትን መጋበዝ፥ የፖለቲካ ተቃዋሚን ሁሉ እንደ ደመኛ ጠላት መቁጠር፥ ትንሽ ልዩነት ያንፀባረቀን ሁሉ ከለየለት ታቃዋሚ ማምታታት፥ ልዩነት ማሰማትን እንደ ክተት አዋጅ ማየት፥... እነዚህ ሁሉ የዚህ አስከፊ ቅርስ ነፀብራቆች ናቸው::

በዚህ ያልተቋረጠ የወከባና የፍዳ ታሪክ፥ በተለይ ለፖለቲካ ሥልጣን ባለማቋረጥ በተካሔዱ ግጭቶች ሳቢያ፥ ላለፉትና አንድም ጊዜ ቢሆን ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ባላየንባቸው ሁለት ክፍለ ዘመናት ኢትዮጵያችን በተከታታይ የአሥር ዓመታት ዕድሜ ሰላም ሳትታደል ቆይታለች:: በዚህ ረጅም ታሪክ ዘመን ሕዝባችን ያሳለፋቸው የእፎይታ ወቅቶች ቢኖሩ ተቀናቃኞቻቸውን በጦር ሜዳ አሸንፈው ሥልጣን የጨበጡ ኃይሎች ኅብረተሰቡን በሙሉ ያቸነፉ እየመሰላቸው እነሱም በተራቸው ወደ ታሪክ ትቢያነት እስኪወርዱ ድረስ በተሸናፊዎች ላይ የጫኑት እርቅ-አልባ ሰላም እንጅ በድርድርና በመግባባት ኅብረተሰባችን በሙሉ በአቸናፊነት የወጣበት ለሁሉም የሚሆኑ የእፎይታ ወቅቶች አልነበሩም::

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሳ.ቁ 18573 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
P.O.Box 18573 Addis Ababa, Ethiopia
ስልክ ቁጥር(Tel.No) 2511-574719;(Fax) 2511574720

ሰሜን አሜሪካ (North America)
P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246, U.S.A
(Tel.No) 202-291-4217 (Fax) 202-291-7645

ዛሬ እኛ የኢትዮጵያ አገር ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕዝባችን ከዚህ ከጦር ድል ከተገኘ ማንአህሎኝነት አጥፊ አዙሪት እንደማይወጣ ተምረንና ተረድተን፤ የሰላማዊ ዴሞክራሲያዊ የትግል አማራጭ አንግበን በመንቀሳቀስ ላይ ነን። በጊዜኣዊ ወታደራዊ ድል ተመርኩዞ ዘላቂ ሰላምን ማስፈን፥ በተጭበረበረና በተድበሰበሰ የፖለቲካ ሂደት ዴሞክራሲን መገንባት እንደማይቻል ጠንቅቀን አውቀን ለነፃና ፍትኃዊ ምርጫ እውንነት ስንዋደቅ ቆይተናል። የኅብረተሰቡ አንዱ ክፍል በአቸናፊነት ሌላው ክፍል ደግሞ በተሸናፊነትና በመብት-አልባነት ተቆላልፈው እስከተያዙ ድረስ ሁኔታዎችን ለቀጣይ ዙር ግጭቶችና አለማረጋጋት ማመቻቸት እንደሆነ የሩቁም ሆነ የቅርቡ ታሪካችን ያረጋገጠልን ሃቅ በመሆኑ ለብሔራዊ እርቅ ስንታገል አሥር ዓመታት አስቆጥረናል።

የግንቦት ወር ፲፱፻፺፯ ዓ/ም የምርጫ ሂደት ከእኛ አልፎ ለመጭው ትውልድ ሲዘከር የሚኖርበት ዋና ምክንያት እነዚህ የሰላማዊ ዴሞክራሲያዊ ለውጥና የብሔራዊ እርቅ እሴቶች በግንባር ቀደምነት ከተሰለፍነው ታጋዮች አልፈው በኅብረተሰባችንም ስርፀው በመግባታቸውና ሕዝባችን ለዘመናት ተቆላልፈን የቆየንበትን አጥፊ አዙሪት ሰባብሮ አዲስ ምዕራፍ የከፈተበትና አዲስ ተስፋ የፈነጠቀበት የሕዝባዊ ድል ሂደት መሆኑ ነው።

የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሕዝብ ድል ከነባሩ የአመፅ የፖለቲካ ባህል ተላቆ፥ በገዥው ፓርቲ የምርጫ ቦርድ ሳይሆን በራሱ ሰላማዊ ትግልና በራሱ የተባበረ ድምፅ ኃያልነት ብቻ ተማምኖ እኛንም ባኮራ፥ የውጭውንም ዓለም ባስደነቀ መልክ የምርጫ ሂደቱ ውስጥ በሙሉ ልብ በመሳተፉ ሆኖ እናገኘዋለን። ሕዝባችን በዚህ መልክ ለነባሩ አጉል ባህል ጀርባውን ሰጥቶ በመንቀሳቀሱ በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ በአመፅ ሳይሆን በሰላማዊ ተጋድሎ መላው ዓለም እየታዘበ የመንግሥት ለውጥ ማምጣት የሚችል ተግባር በመፈጸም የቆየውን የጥፋት አዙሪት ሰብሯል። ሆኖም ግን እንደዚህ እየተሰበረ ያለውን የጥፋት አዙሪት ጥቂት የኢሕአዴግ መሪዎች መልሰው ለመግጠም የሕዝባችንን ድምፅ በጠራራ ፀሐይ ሰርቀው የሸፍጥ ድላቸውን ማወጃቸው ይኽንን ታሪካዊ ሃቅ ምንም አይቀይረውም። ሕዝባችን የንፁህ ልጆቹ ደም በአደባባይ እየፈሰሰም ቢሆን " በሰላማዊ ሂደትም፥ በምርጫም ለውጥ አይቻልም " የሚል የጥፋት መደምደሚያ ላይ ደርሶ እነሱ እንደተመኙት አስከፊ ወጥመዳቸው ውስጥ አልወደቀላቸውም።

ሁለተኛው ታሪካዊ ድል እዚህ ላይ ነው። በመስዋዕትነትና በሰላማዊ ትግል ያገኘውን ድል ለማስመለስ ሕዝባችን በአመፅ የተሰማሩበትን ጥቂት አምባ-ገነኖች በአመፅ ሊቋቋምቅቸው አልተነሳም። አሁንም እንደ ቅድመ-ምርጫው ወቅት በአንድነቱና በኃያልነቱ ተማምኖ አመፀኞቹን በሰላማዊ የሰላም ትግል፥ ሕገ-ወጦቹን በሕጋዊ ትግል ስትራቴጂ ለመቋቋምና ለዚህም የተጠየቀውን ማንኛውንም መስዋዕትነት ለመክፈል ቁርጠኛነቱን እያሳያቸው ይገኛል። " ሥልጣን በምርጫ " ካሉ በኋላ ምርጫው ሳይቀናቸውና ውጤቱ ሳይጥማቸው ሲቀር ወዳልተላቀቃቸው ነባሩና ያረጀ ያፈጀ " ልጣን በአመፅ " ወደሚል ዘይቤ ተመልሰው የተዘፈቁት እነዚህ ጥቂት ፀረ-ሕዝቦች ብቻ እንጅ ኅብረተሰባችን አይደለም። የራሳቸውን የሥልጣን ጥም ለማርካት የሚያካሂዱትን መፍጨርጨር በአጠቃላይ ለኢሕአዴግ አባላትና ደጋፊዎች ከዚያም አልፈው ለታጋሹና እንደተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ወገኑ ላላባራ ስቃይ ለተዳረገው ሰፊ የትግራይ ሕዝብ የምት ሽረት ጥያቄ አስመስለው በማቅረብ፥ ቀቢፀ-ተስፋነት ብቻ ሊሰጠው በሚችል የአጥፍቶ ጠፊ ጉልበት እየተንቀሳቀሱ የጥላቻ መርዝ የተላበሰ ፕሮፓጋንዳቸውን በመንዛት ላይ ታች በማለት አጉል ሲባዝኑ አየናቸው። እዚህም ላይ ኅብረተሰባችን " እንመራሃለን " ከሚሉት ጥቂት ኋላ-ቀር ኃይሎች ምን ያህል ልቆ የተራመደ መሆኑን ያረጋገጠበት ሌላ ሦስተኛ ድልን ተገናጽፏል።

ይኽ ሦስተኛው ድል ከነባሩና ከአስከፊው አዙሪት ሰብሮ በመውጣት ድል አድራጊው ሕዝባችን አሁንም በረጅሙ ታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ አቸናፊዎችንም ተቸናፊዎችንም ለሚያካትት የሰላምና የዴሞክራሲ ሂደት በመቆም የብሔራዊ " የብሔራዊ አንድነት የሽግግር መንግሥት " እንዲቋቋም አገር-ወርዳድና ዴሞክራሲያዊ ልጆቹ ያቀረቡትን የቀውስ መውጫ አሳብ በሙሉ ልብ በመቀበሉ የተጎናፀፍነው ድል ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ይኽንን ታሪካዊ ጥሪ በመቀበል ከኢሕአዴግ አባላትና ደጋፊዎች አልፎ ለሚያዋክቡት፥ ለሚገድሉት፥ የንፁህ ልጆቹን ደም በጠራራ ፀሐይ ለሚያፈሱት፥ ለሚያንገላቱትና ነጋ ጠባ ለሚያዋርዱት ለኢሕአዴግ መሪዎችም የእርቅ እጁን በመዘርጋት በአኩሪ ታሪኩ ላይ ጠባሳ ሆኖ የቆየውን በአቸናፊዎች የሚጫንን የእርቅ-አልባ ሰላምና ድል ሂደት ለአንዴና ለዘለዓለም አንቅሮ የተፋው መሆኑን ኅሊና ላለው ሁሉ በማያሻማ ሁኔታ አረጋግጧል።

እነዚህ ሁሉ በትግልና በመስዋዕትነት የተገኙ ድሎች በቋፍ ያሉ ድሎች ናቸው። እያከተመ ያለውን ክፍለ-ዘመን ከነደምና እንባው አራግፈን በአዲስ መንፈስ ወደ አዲስ የኢትዮጵያ ክፍለ-ዘመን ለመሸጋገርና አዲስ የሰላም፥ የአንድነትና የብልጽግና ዘመን ለመጀመር ከተመኘን እየተሰበረ ያለው አዙሪት መልሶ ገጥሞ እንደገና በአመፅ፥ በጭቆናና በድህነት ኋላ-ቀር አዙሪት ውስጥ እንዳንዘፈቅ ከፈለግን ብዙ አማራጮች የሉንም። የጥፋት አዙሪቱ መልሶ መግጠም እንዳይጀምር የተፈለገውን መስዋዕትነት ሁሉ እየከፈልን ታሪካዊ ድላችንን መንከባከብ ይገባናል። እኛ የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር-ወዳድ ኃይሎች ይኽንን ድል ከሕዝባችን ጎን ሆነን እንንከባከበዋለን።

ይኽ የኢትዮጵያ ሕዝብና የታጋይ ኃይሎቹ ታሪካዊ ተጋድሎ " ድምፃችን ይከበር " ከሚል ቀጭን የምርጫ ውጤት ላይ ካተኮረ መፈክር እጅግ አልፎ የሚሄድ ተጋድሎ ነው። ከዚህ ዘልቀን ኅብረተሰባችን <u>"ለውጥ በሰላም፥ ሰላም በእርቅ፥ እርቅ ኅብረተሰቡን በሙሉ ባካተተ ድል"</u> በሚሉ አዳዲስ እሴቶች ሥር ተሰልፎ የሚያካሂደው ትግል ነው። ከቆዩን ካረጁና እነሱም እንደ ክፍለ-ዘመኑ ከመሸባቸው ኋላ-ቀር አስተሳሰቦችና ከነሱ አራማጆች ጋር " ድላችን ይከበር " የሚል መፈክር አንግበን የምናካሂደው ታሪካዊ ትንንቅ ነው። በዚህ መልክ ኅብረተሰባችን የተጎናፀፈውን ድል እንድንንከባከብ የሚገፋፋን ለኢትዮጵያችን ከአዲስ ክፍለ-ዘመን ጋር ለአዲስ ብሩኅ ተስፋ ያለን ጉጉት ብቻ አይደለም። እንደማንኛውም ገና በቋፍ ያለ ድል ይኽንንም ጥቂት የሥልጣን ጥመኛና ያከተመ ዘመን ኃይሎች በአመፅ እንዲፈታተኑትና እንዲቀለብሱት ከፈቀድንላቸውና ሕዝባችን ታግሎና ተሰውቶ ያገኘውን ድል በሸፍጥና በአመፅ መልሶ ከተነጠቀ ሰላም፥ ዴሞክራሲ፥ ምርጫ፥ ወዘተ.... በሚባሉ እሴቶች መጨረሻው ለማይታይ ረጅም ጊዜ ተስፋ የሚቆርጥበትና የተገላገልናቸው የመሰለን የጥፋት አዙሪቶች ውስጥ መልሰን የምንዳክርበት ከባድ አደጋም እንዳለ ጠንቅቀን ስለምናውቅ ነው።

እኛ የኢትዮጵያ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች ከዚህ መሠረታዊ ሃቅ በመነሳት ኅብረተሰባችን የተጎናፀፈውን ታሪካዊ ድል ላለማስነጠቅ በማሳየት ላይ ካለው ወኔ የሚመጥን የዓላማ ፅናት እንደሚጠበቅብን እንገነዘባለን። በዚህ ቀውጢ ቀን ሕዝባችን ከሚያንፀባርቀው የአመራር ጥማት የሚመጥን የትግል ስትራቴጅ ጥራት ወሳኝ በመሆኑም ታሪክና ሕዝብ ለጣሉብን አደራ ብቁም ዝግጁም መሆናችንን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማብሰር ይጠበቅብናል። በዚያው ልክ ደግሞ ለኢትዮጵያችን ወሳኝ በሚሆኑት በሚቀጥሉት ሳምንታትና ወራት በሕዝባችን ወኔ እየተበረታታን የምንያያዘው አዲስ የትግል ምዕራፍ ከፖለቲካ ድርጅቶች አልፎ በአጠቃላይ ኅብረተሰቡን፥ በነጠላ ደግሞ እራሱን/እራሷን እንደዚች አገር የቁርጥ ቀን ልጅ የሚቆጥርን እያንዳንዱን/እያንዳንዷን የኢትዮጵያ ዜጋ የሚመለከት ታሪካዊ የትግል ምዕራፍ ውስጥ ገብተናል ብለን እናምናለን።

ከዚህ በመነሳት በቅንጅቱና በኅብረቱ አነሳሽነት ለመስከረም ፳ እና ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም በሕገ-መንግሥቱ ማዕቀፍ ውስጥ የሕዝባችንን ድል ለማስከበር ስለሚካሄደው ሰላማዊና ሕጋዊ ቀጣይ ትግል ለመምከር የፖለቲካ ድርጅቶች፥ የተለያዩ የሙያ ማኅበራት፥ የሴቶች፥ የወጣቶችና የተማሪዎች፥ የባህልና የሐይማኖት ስብስቦች ተወካዮች፥ ከየአካባቢው የሚጋበዙ የአገር ሽማግሌዎች፥ ወዘተ..... የሚሳተፉበት አንድ ታላቅ "የሰላም፥ የዜጎች አንድነት ትስስርና የዴሞክራሲ አገር-አቀፍ ጉባዔ" እንዲጠራ ተደርጎ የነበረው ሙከራና በማግስቱም መስከረም ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ/ም ታቅዶ የነበረው ከአዲስ አበባ ጀምሮ በአገሪቱ

ባሉ ታላላቅ ከተሞችና በዓለም-አቀፍም ደረጃ ታቅዶ የነበረው ሕዝባዊ "የሰላም፥ የዜጎች አንድነት ትስስርና የዴሞክራሲ የድጋፍ ሰልፍ" የሕዝቡን የተደራጀና የተቀነባበረ ተጋድሎ ከጦር አብልጦ በሚፈራው ኢሕአዴግ ተጨናግፈዋል፡፡ በመቀጠል ተጠርቶ የነበረው ቤት ውስጥ ተከትቶ በመቀመጥ ተቃውሞን የማሰማትና የመግለጽ ጥሪ በድርድር ስም ተግባራዊ ሳይሆን ቀቷል፡፡ በተያያዘ ሁኔታ በፍጥነት እየተለዋወጠ የሚሄደው የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ በአንድ በኩል የኢሕአዴግ መሪዎች ጊዜ ለመግዛትና የሕዝቡን ትግል አደናግሮ ለማዳከም ባላቸው ምኞት ቀርቦ የነበረው የድርድር ጥሪ በእነዚሁ ጥቂቶች ሃላፊነት የጎደለው ግትር አቋም ተደናቅፎ ተቋርጧል፡፡

በተጭበረበረ ድል በፓርላማ አብላጫ ድምፅ አግኝቻለሁ በማለት የኢሕአዴግ መሪዎች ይኽንን ፓርላማ ሰብስበው አዲስ የሚሉትን ለቀጣዮቹ አምስት ዓመታት በሸፍጥ የተወለደና በእርግጥም ከእንግዲህ በአስከፊ አመፅ ብቻ ፀንቶ ሊቆይ ለሚችል መንግሥታቸው ዝግጅታቸውን አጠናቀዋል፡፡ መስከረም ሰላሳ ቀን ፓርላማው እንደሚሰየም አውጇል፡፡ በዚህ ጉዳይ ኅብረታችን አስቸኳይ የስልክ ተከታታይ ጉባዔዎች አድርጎ ቀደም ሲል በሁለተኛ መደበኛ ጉባዔው ላይ በደረሰበት የምርጫውን ውጤት አለመቀበልና ከመሰል አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር በመሆን የሕዝብ ድምፅ እንዲከበር ጠብቆ መታገል በሚለው አቋሙ በመጽናት <u>በዚህ ሕገ-ወጥ ፓርላማ ላለመግባት በድምፅ ብልጫ ወስኗል፡፡</u>
በኅብረቱም የተካተቱ ድርጅቶች ሆኑ ሌሎች በዚህ ፓርላማ ውስጥ እንሳተፋለን ቢሉም ይኽ ውሳኔአቸው የተቃዋሚውን ጎራ ግራ አጋብቶና ከፋፍሎ ለጥቃትና ለሽንፈት እንዳይዳርገው ከሁሉም ወገን ከፍተኛ ጥንቃቄና ብስለት የሚጠበቅበት አዲስ የትግል ምዕራፍ ውስጥ እንገኛለን፡፡

በእኛ ግምት ለቀጣዩ ትግል ጥራት ያለው አንድና አንድ ብቻ ዋስትና የግንቦት ድሎች ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ዜጎች ሁሉ የተወሰኑ ዜጎች በፓርላማ ውስጥ ሆነው ሊያካሂዱ የፈለጉት ትግል ከአጠቃላዩ ተጋድሎ ውስጥ በጣም አነስተኛ ቦታ እንዳለውና ዋናው ትግል በጠቅላላው በኅብረተሰቡ ታጅቦ የሚደረገው ሰላማዊና ሕጋዊ ትግል እንደሆነ መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ በመነሳት የፓርላማ መግባት አለመግባቱ ጉዳይ ኢሕአዴግ እንደሚያልመው የክፍፍል፥ የውዥንብርና የድክመት ምንጭ እንዳይሆን አስፈላጊውን ጥንቃቄ እያደረጉ አዲሱን የትግል ምዕራፍ ለመያያዝ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች፥ የሲቪክ ማኅበረሰቡ ተወካዮች፥ የሴቶች፥ የወጣቶች፥ የተማሪዎች ስብስቦች፥ በጠቅላላው ሕዝባችን በነቂስ፥ በአንድነት <u>"ዜጎች ለግንቦት ድሎች"</u> በሚል አርማ ሥር በመሰባሰብ በከፍተኛ ደረጃ መንቀሳቀስ ይጠበቅብናል፡፡ ኅብረታችን ከቅንጅቱ ወገኖቻችንና ከሌሎች አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች መክሮ በጥቂት ቀናት ውስጥ ቀጣዩ የሕዝባችን ሰላማዊና ሕጋዊ ትግል ስለሚከተለው ሂደት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተጨባጭ የሆኑ አሳቦችንንና እርምጃዎችን ለማቅረብ ቃል ይገባል፡፡ በመሆኑም ይኽ እስኪሆን ድረስ አዲሱን የትግል ምዕራፍ በመላ ኅብረተሰባችን በታጀበ እንቅስቃሴ ለመክፈት እንዲቻል፤

1ኛ. የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 104/1 በፌዴራልና በክልል የምርጫ ክልሎች ነፃና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኝነት እንዲያካሂድ ከማንኛውም ተፅዕኖ ነፃ በሆነ ሁኔታ ሃላፊነቱን እንዲያከናውን አደራ የጣለበት ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ሕገ-መንግሥቱን በመጻረርና ሃላፊነቱን በመጣስ በወገናዊነትና ካለው ገዥ ፓርቲ ጎን ቆሞ የምርጫውን ሂደት ከዳር እስከ ዳር የበከለው መሆኑን ተገንዝቦ ሕዝባችን የተቃውሞ ድምፁን ማሰማት እንደሚያስፈልገው በማመን፤

2ኛ. በአጠቃላይ የምርጫው ሂደት የሕዝብ አመኔታ ባላገኘበትና በዓለም-አቀፍ ደረጃም በእርግጥ ገለልተኛ የሆኑ ታዛቢዎችም በአንድ በኩል የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዴሞክራሲ ካለው ጉጉት በማይመጥን፥ በሌላ በኩል ደግሞ በነፃ ምርጫ ጉዳይ በዓለም-አቀፍ ደረጃ የታወቁትን መሥፈርቶች ባላሟላ ሁኔታ የተካሄደ መሆኑን ማጋለጣቸውን መልሶ ማስታወስ አገራዊ ግዴታችን መሆኑን በማጤን፤

3ኛ. ከዚህ ከዳር እስከ ዳር በተጭበረበረና በኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ በዓለም-አቀፉ ኅብረተሰብ ፊት እውቅና ባላገኘ ውጤት ላይ ተመስርቶ የሚቋቋመው ፓርላማም የአገሪቱ ሕገ-መንግሥት በአንቀፅ 54/1 *"የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ሁሉን አቀፍ፥ ነፃ፥ ቀጥተኛና ትክክለኛ በሆነና ድምፅ በሚስጢር በሚሰጥበት ሥርዓት በየ አምስት ዓመቱ በሕዝብ ይመረጣሉ"* ተብሎ የደነገገውን አንቀፅ በመጣስ የአገሪቱን ሕገ-መንግሥት ተፃርሮ የተሰየመ በመሆኑ ሕዝባዊና ሕጋዊ ተቃውሞ ማስመዝገብ ለቀጣዩ ትግል አስፈላጊ መሆኑን በማሰብ፤

4ኛ. ከዚህ ከጽንሱ ፀረ-ሕገ-መንግሥት በሆነ መልክ የተሰየመ ፓርላማ በሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ 56 እና አንቀፅ 73 መሠረት ተጠቅሞ የፌዴራል መንግሥቱን የሕግ አስፈጻሚ አካል የማደራጀትም ሆነ በምክር ቤቱ ውስጥ አብዛኛውን መቀመጫ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ ድርጅቶች ከምክር ቤቱ አባላት መኻከል ይመርጣል የሚሉትን አንቀፆች በተግባር ለማዋል <u>የሞራልም ሆነ ሕጋዊ ብቃት ስለሌለው</u> በዚህ ምክር ቤት የተሰየመ መንግሥትም ሕገ-መንግሥቱን በተፃረረ መልክ የሚቋቋም መንግሥት መሆኑን መዝግቦ ሕዝባዊ ተቃውሞ በይፋ የማስታወቅን አስፈላጊነት በመገንዘብ፤

5ኛ. ባለፉት ወራት የሕዝባችን ድምፅ ይከበር ብለው የግንቦትን ድሎች ለማስመለስ ሲንቀሳቀሱ ለጋ ሕይዎታቸውን ለሰውት የኢትዮጵያ ልጆችና ለፈሰሰው የወላጅ እንባ ፍትኅ የመጠየቅ መብታችንና ብሔራዊ ግዴታችን እንደተጠበቀ ሆኖ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰማዕትነታቸውን በአክብሮት አስቦ መዋሉ የሞራል ግዴታው መሆኑን በማሰብ፤

6ኛ. ዓለም-አቀፉ ኅብረተሰብም ይኽ የኢሕአዴግ የምርጫ ሂደት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዴሞክራሲ ካለው ጉጉትና በመላው ዓለም ከፀኑ የነፃና የርቱኣዊ ምርጫ መስፈርቶች የማይመጥን መሆኑን በይፋ ባስታወቀበት ሁኔታ እኛ ኢትዮጵያውያን የውጭው ዓለም ያጥላላውን ውጤት አለመቀበላችንና ድላችንን ለማስመለስ የቆረጥን መሆናችንን ለመላው ዓለም ማስታወቁ የአገር ክብር ጉዳይም መሆኑን በመገንዘብ፤

7ኛ. የተወሰኑ ተመራጮች በዚህ ፓርላማ ውስጥ መሳተፍ በአንድ በኩል የኢትዮጵያ ሕዝብ ይኽንን ውጤት ተቀበለ ማለት እንዳልሆነ ማሳየትና ከሁሉም በላይ ደግሞ ትግሉ የከሰመ ለሚመስላቸው አንዳንድ ወገኖች በሕዝባዊነቱና በቅንብሩ ደምቆ ወደ አዲስና ከፍተኛ ምዕራፍ እየተሸጋገረ መሆኑን ለኢሕአዴግ መሪዎችም ሆነ ለዓለም-አቀፉ ማኅበረሰብ በማያሻማ ሁኔታ ማስጨበጥ አስፈላጊ ብሔራዊ ግዴታ መሆኑን በመረዳት፤

የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብን የግንቦት ድሎች ለማስከበር <u>"ዜጎች ለግንቦት ድሎች"</u> በማለት የምንያያዘው ተጋድሎ በዳግም ድል ይቋጭ ዘንድ ለቀጣዩ አዲስ የትግል ምዕራፍ ቅንጅቱና ኅብረቱ ከሌሎች የሲቪክና የሙያ ማኅበራት ጋር ተመካክረው በቅርቡ ለሚጠሩት ቀደም ሲል ተደርገው የነበሩ የቤት ውስጥ ክተት ጥሪ ዓይነትም ይሁን ሌሎች ማናቸውንም ተመሳሳይ የሰላማዊ ትግል የትብብር ጥሪዎች ሕዝባችን ከዳር እስከ ዳርና በነቂስ ተሳታፊነቱን እንዲያሳይ ዝግጁ እንዲሆን በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!
የኢትዮጵያ ሕዝብ በተባበረ ሰላማዊ ትግሉ የተነጠቀ መብቱን ያስከብራል!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
መስከረም ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፯